# ተስፋዬ ገብረአብና ሁለቱ ዝሆኖች

ከእጅጋየሁ አወቀ

ተስፋዬ ገብረአብ በቅርብ ጊዜ ያሳተሙትን ‘የደራሲው ማስታወሻ’ አነበብሁ። ሌሎች ሥራዎቻቸውንም አንብቢያለሁ። የመጻፍ ችሎታቸውን አደንቃለሁ፤ የመጽሐፎቻቸውን ግብ ግን እጠራጠራለሁ። የመለስ/ወያኔ ባለሥልጣናትን የሚያጋልጥ ምስጢር ይፋ በማድረግ ለተቀዋሚዎች ትግል አጋዥ በመምሰሉ ተቀዋሚዎችን ሊያረካ የሚችል ቢሆንም፣ ራሳቸውን ተቀዋሚዎችን የማዳከም ተልዕኮ ይኖረዋል ብየ እሰጋለሁ። ‘የደራሲው ማስታወሻ’ የተስፋዬ ማስታሻ ነው-እሳቸው እንደሚሉት በወያኔ አገልጋይነታቸው ዘመን የያዟቸውን ብጭቅጫቂ ወረቀቶች ገጣጥመው የጻፉት ትረካ። ማስታወሻ (ትረካ) በጊዜና በቦታ ተወስኖ የሆነንና ያልሆነን አንድ ክስተት ሳይቀንሱ ሳይጨምሩ አንዳለ ማስቀመጥን ይጠይቃል-ሀቀኛ መሆንን፤ የጥላቻና መውደድ ተጽዕኖ ካልበከለው ግላዊ ስሜት ነፃነትን። ባጭሩ እውነት መሆን አለበት ማለት ነው። ተስፋዬም ተረት (ልብወለድ) ሳይሆን አንድን የሆነና ያልሆነ ድርጊት *ልተርክ* ካሉ ከስሚታዊነት፣ ከጥላቻና ከወዳጅነት ተጽዕኖዎች ነፃ ሊሆኑ ይገባል። እንደ አንድ የተዋጣለት ደራሲ የግል ስሜትና ውሸት ሳይደባልቁ እውነትን በመተረክ ረገድ የገለልተኛነት ፈተናን ማለፍ ችለዋል ብየ ለማመን ተቸገርኩ።

ተስፋዬ ለኢትዮጵያና ህዝቦቿ የሚቆረቆሩ ሀገር ወዳድ፣ ስለተተኪው ትውልድ ዕጣ ፈንታም የሚጨነቁ በሚመስል ስለራሳቸው ገልጠዋል፤ ምክርም ለግሰዋል። ጥሩ ነበር እንዲያ ቢሆኑ-ኢትዮጵያ ያሳደገቻቸው ሀገር ናትና። በበኩሌ አገሬ ብለው ለሀገሪቱ ጥቅም እስከሠሩ ድረስ የኤርትራ ደም ኖራቸውም አልኖራቸው ኢትዮጵያዊ ወገኔ ናቸው ብየ አምናለሁ። ሌሎች ኤርትራውያንንም የማየው እንዲሁ ነው፤ ጥላቻ የለኝም። ግን እንደተስፋዬ ዓይነቱ ተወልዶ ባደገበት ሀገር እና በወላጆቹና ዘመዶቹ ሀገር መካከል ያልተፈታ ጠብ በዘለቀበት እና ሌሎችም ውስብስብ የግንኙነት ክሮች በሀገር ጥቅምና ደህንነት ላይ ጉዳት ወይም የጉዳት ስጋት የሚያደርሱ መስለው ሲታዩ፣ ከተለመደው ውጭ ብርቱ ጥንቃቄና ጥርጣሬ ማድረግ በየትኛውም ሀገር ያለ ነውና መጠንቀቁንና መጠርጠሩን እደግፋለሁ።

በሰላም ሆነ በማናቸውም ዓይነት አሻጥር ጉዳት የሚያደርሱ ሰዎች የተለያየ ካባ ልብሰውና አስመስለው በማሳሳት ጭምር መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም። ዜጋ ከሆኑበት አገር ይልቅ ለትውልድ (ዝርያ) አገራቸው የበለጠ ታማኝ በመሆን (መሆንም ያለ ነው) ዜጋ የሆኑበትን አገር የጎዱም፣ የሚጎዱም አሉ። ይህን የሚያደርጉት ‘ከጳጳሱ ቄሱ’ እንዲሉ ራስን ከእውነተኛው ዜጋ የበለጠ ለሀገር ተቆርቋሪ፣ የህዝብ ጠበቃ አድርጎ ቀድሞ በመናገርና በማሳሳት ጭምር መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም። ራስን ከማናቸውም የሚያስጠረጥር ነገር ውጭ ለማድረግ በአንደበታቸው የሚናገሩትና የሚጽፉት በስውር ከሚያደርጉት የግድ ተቃራኒ ይሆናል-ስውር ተልዕኮው ቢታወቅ የሚከፈለው ዋጋ እጅግ ከባድ ነውና።

እንደተስፋዬ መሰል የሚደነቅ የስነ ጽሁፍ ሙያ ያለው ሰው በእንዲህ ዓይነቱ ተግባር ከተሰማራ ሥራውን የሚያደንቅ ብዙ ሰው ሰለሚኖረው ተልዕኮውን ለመተግበርና አድማጭም ለማግኘት ብዙ ችግር አይገጥመውም። በጦር መሳሪያ ከሚያጠቃ ጠላት ይልቅ በዚህ ዓይነት ስልት ህዝብን በመከፋፈልና አንድነቱን በመናድ የሚያደርሰው የማዳከም ጉዳት አደገኛ ነው፤ ቀጣይነትም ይኖረዋል። የደራሲ ተስፋዬ ሙያና ችሎታ እንዲሁም ያዳበሩትና የተካኑት የህዝብን አንድነትና ህብረት የማላላት ረቂቅ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ልምድ አደገኛነት ቸል መባል የለበትም። የአፈጮሌና መሰሪ ፕሮፓጋንዳ መሳሪያ በመሆን ራሳችን በራሳችን እንዳንጎዳ መጠንቀቅ ይኖርብናል። እውነቱን ከውሸት ለመለየት የደራሲውን ማንነትና ምንነት፣ ለምን ያሉትን እንዳሉና በሚጽፉበት ጉዳይ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያላቸውን ትስስርና ተቃርኖ ጭምር ልንጠይቅ ይገባል። ከአፈ-ጮሌ አንደበት የወጣውን እንዳለ ወስዶ ከማዛመትና ከማራገብ በፊት መመራመር ሊቀድም ይገባል። የተስፋዬ ኢትዮጵያዊነትን መሻት ከልብ ሊሆን ይገባል። ሀገር ወዳድ ‘ታማኝ ዜጋ ነኝ’ ብሎ ከማንቧረቅ በላይ በተግባር ለሀገር ጥቅም ቆሞ መገኘትን፣ ለሀገሪቱ ያላቸው ታማኝነት ጥያቄ የማያስነሳ ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል።

ደራሲው በተለይ ‘ሁለቱ ዝሆኖች’ በሚለው ምዕራፍ[1] ስር የጻፉት እና አከታትለውም በፓልቶክ[2] አማካኝነት ለህዝብ የገለጡት ብዙ ጥያቄዎችን የሚጭሩ ነገሮች አሉባቸው። የሁለቱ ዝሆኖች ዋናው የፍልሚያ መስክ የኤርትራ ጉዳይ ነው።

---

[1] ተስፋዬ ገብረአብ፤ የደራሲው ማስታወሻ፤ ፳፻፪ ዓ.ም. ገጽ ና ፶፯-፸፫

[2] ለምሳሌ http://ecadforum.com/blog/?p=3643

ለጠቡ መነሻ የሆነውን በየአጋጣሚው ሁለቱም ተፋላሚዎች ጭምር ሳይቀሩ የገለጡት ስለሆነ ብዙም ከህዝብ የተሰወረ አይደለም። ይሁን እንጅ ዛሬ ከአስር ዓመታት በኋላ ኤርትራን በሚመለከት፣ በሌላ ሳይሆን በኤርትራዊው ተስፋዬ ሲነገረን ቢያንስ የምንጠብቀው ዓቢይ ነገር አለ- ገለልተኛነትና ማስረጃ። ገለልተኛነታቸው ጥያቄ ላይ በወደቀበት በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጉዳይ ጎራ ለይተው ዋና ተዋናይ በሆኑት ዝሆኖች ስብእና እና ባህርይ ላይ ለመጻፍ ተስፋዬ ባልከጃሉ፤ ከከጀሉ ደግሞ ብርቱ ጥንቃቄ ባደረጉ፣ ሚዛን በጠበቁ ነበር። ደራሲው ግን እጅግ ደፋር ስለሆኑ ከነሰሜታዊ ኮተታቸው ዘው ብለው በመግባት በራሳቸው የሰላ ብዕር ሳያስቡት ራሳቸውን አጋልጠዋል። ሰልፍና ሚናቸውን በውል አሳይተዋል። የኛን የአንባቢዎችን እውቀትና ብይን የመስጠት ችሎታም ተፈታትነዋል።

ኤርትራ ኢትዮጵያን ከወረረች በኋላ ጦሯን ፊት ወደነበረበት እንድትመልስ፣ ካልሆነ ግን ለመልሶ ማጥቃት ኢትዮጵያ እንድትዘጋጅና ዝግጅቱም ተግባራዊ እንዲሆን የሚለውን ሃሳብ በመሪነት ያራመዱት (አንደኛው ዝሆን) አቶ ስየ ናቸው። የሁለተኛው ቡድን መሪ አቶ መለስ (ሌላው ዝሆን) ኤርትራ ልትወረን እየተዘጋጀች ነውና ለመከላከል እንዘጋጅ የሚለውን ሃሳብ ከማጣጣል ጀምሮ፣ ከወረራ በኋላም የጦር መሳሪያ ግዥ እንዳይከናወን የተለያዩ መሰናክሎችን በመፍጠር፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት መስዋዕትነት ከፍሎ ግዛቱን ነፃ እንዳወጣ ሠራዊቱ ወደፊት ገስግሶ የኤርትራን ሠራዊት እንዳይደመስስ እንቅስቃሴውን በማቆም፣ በአሰብ በኩልም እየገሰገሰ ያለው ጦር አሰብን እንዳይዝ በማድረግ፣ ሠራዊቱ ያገኘውን ድል በአልጀርስ ድርድርና ሊያስረታ የሚችል የፈረሰ የቅኝ ግዛትን ውል ሄግ ላይ ለተሰየመው ፍ/ቤት በማቅረብ ዋናው ጦርነት የተካሄደበትን ባድመንና ሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶችን በሄጉ ፍ/ቤት ውሳኔ ለኤርትራ እንዲሰጥ አስደርገዋል። በዚህም አቶ መለስ ለኤርትራ ውለታ ውለዋል ተብለው በብዙዎች ዘንድ ሲከሰሱ፣ አቶ ስየ ደግሞ በጦረኝነትና በኤርትራ ጠላትነት እንዲፈረጁ ሆነዋል። ይህ የኤርትራ ጦርነት ጉዳይ የወያኔን አመራር ሁለት ከፍሎ፣ ለኤርትራ ደህንነትና ጥቅም እንደቆመ የሚታማው በአቶ መለስ የሚመራው ቡድን እጁ የነበረውን የመንግሥት ስልጣን ተጠቅሞ ሲያሸንፍ፣ ለኢትዮጵያ ጥቅም የታገለው የአቶ ስየ ቡድን ከፓርቲ አመራርነት ከመወገዱም በላይ ለአቶ ስየና ቤተሰባቸው ህገወጥ እስር ምክንያት ሆኗል። ይህን ሀቅ ሁላችን እናውቃለን።

ከሁለቱ ዝሆኖች በስተጀርባ ይህ ሁኔታ እያለ፣ አቶ ተስፋየ ስየንና መለስን ሲያነጻጽሩ ኤርትራዊ ወገናቸው አቶ መለስን በሚመለከት እምብዛም አዲስ ነገር ሳያክሉ ህዝብ የሚያውቀውን አስቀምጠዋል። ደራሲው በተለይ ሁለቱን ዝሆኖች በሚመለከት በኢሲኤዲኤፍ[3] የውይይት መድረክ ላይ እንዳብራሩት አዲስ መረጃ አገኘሁ የሚሉት አቶ ስየን በሚመለክት ነው። ስየ *"እንደትንሹ ቡሽ ገገማ ነገር ነው"*፣ ስየ *"ዘነዘና የዋጠ ይመስላል። ከመሬት ተንስቶ ቁጣው አይጣል! ሰዎችን ሁሉ ገና ንቆ ጨርሷል። ከስየ ጋር ለመስራት ከወሰንክ ካዳሚ ለመሆን ጫንቃህን አመቻቸ"*፣ *"ስየ ጀል ድመት"* ነው፣ ስየ *የኤርትራን ህዝብ በጠላትነት ይመለከታል*[4] ይላሉ። ቀጥለውም "በኢትዮጵያዊነት አጀንዳ መለስና ስየ የአንድ ድምቡሎ ሁለት ገጽታ ናቸው" በማለት የማይመሳሰሉ ሰዎችን ለማመሳሰል ሞክረዋል። ከዚህም አልፈው ከባለቤቱና ከአዳማጩ ህዝብ የበለጠ እኔ አውቃለሁ በማለት "'*ስየ ታሰሮ ከተፈታ በኋላ ራሱን ኢትዮጵያዊ ማድረግ ችሏል*' ብለው የሚከራከሩ አሉ" ካሉ በኋላ *"እኔ ይህን ለመቀበል እቸገራለሁ"*[5] የሚል ብያኔ ሰጥተዋል።

ይህ የጥላቻ ስሜት ነጸብራቅ የሆነ የግል አስተያየት እንጅ የማስረጃ ውጤት አይደለም። ብሶትና ቁጣ የወለደው ስድብና ማዋረድ። በፓልቶኩ መግለጫቸው በመጽሐፉ የግሌ አስተያየት የለበትም፣ በአዲስ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ እንጅ ቢሉም፣ ከላይ የተጠቀሰው ዘለፋና ማጥላላት ባልበረደ የግል ጥላቻ ስሜት የቀለመ የበቀለኛ ብዕራቸው ውጤት ነው-የተዛባ፣ ያልተሞረደ፣ ጭፍንና በሃሰት ላይ የተመሰረተ የግል አስተያየት። አንድን ሰው ገገማ፣ ጀል ድመት፣ ዘነዘና የዋጠ፣ ወዘተ ብሎ ክብርና ስብእናውን ዝቅ ለማድረግ የሚያበቃ የሙያ ብቃት የላቸውም፤ የሙያተኛ አስተያየት ከሆነም ማስረጃውን አላቀረቡም። አቶ ስየን በሩቅም ቢሆን ለምናውቅ ሁሉ ዘላፋውን ከመታዘብ በቀር እውነትነት አለው ብለን አንቀበልም። አንድ ሀቅ አለ ራሳቸው ደራሲው ያረጋገጡት "ስድብኤል" መሆናችውን። በስድብኤልነታቸው <u>"ተቀዋሚዎችን በስድብ አፈርድሜ" ማስጋጥ</u>፣ <u>"ኢትዮጵያዊነት የሚል ባንዲራ"</u> <u>የሚያውለበልቡትን መሳደብ</u> *ሥራቸው* እንደነበር ገልጠው፣ "*<u>የጋዜጥኛነት ስራውን በስድብ የጀመረ ሰው እግዚአብሔር ካላገዘው በቀር ከገባበት የስድብ አዙሪት ከሆነ የስድብ ጎርፍ</u>*

[3] http://ecadforum.com/blog/?p=3643

[4] ተስፋዬ ገብረአብ፣ <u>የደራሲው ማስታውሻ፣</u> ገጽ 98ና ተከታዮቹ

[5] ተስፋዬ ገብረአብ፣ <u>የደራሲው ማስታውሻ፣</u> ገጽ 60

*መውጣት አይቻለውም።"*[6] ብልዋል። ተስፋዬ እዚህ ላይ እውነት ብለዋል። ግን ከስድብኤል ተላቅቄያለሁ ይበሉ እንጅ፣ እንዲላቀቁ እግዚአብሔር ገና ስላልረዳቸው አሁንም በተቀዋሚዎችና የኢትዮጵያዊነትን ባንዲራ በሚያውለበልቡ ላይ የስድብ ዘመቻውን እያጧጧፉ ነው። ለመሆኑ አዲስ ማስረጃ አገኘሁ የሚሉት የትኛው ማስረጃ ነው? የታለ የጠቀሱት? እንደአንድ ተአማኒ ጸሀፊ ለምን የግርጌ ማስታወሻ ወይም ዋቢ ማስረጃ አላደረጉም? ልብወለድ ሥራቸውን ከትንሽ እውነት ጋር ቀላቅለው እውነተኛ ታሪክ ነው እያሉ መሿለል አይችሉም። ከኢሕአዴግ/ወይኔ የተካኑትን ያለዋቢ ማስረጃ ወይም ሊታመን የሚችል ተጠቃሽ ምስክር ሳያበጁ የተከበሩ ሰዎችን ስብዕና የማጥፋት ዘመቻ character assassination ማቆም አልቻሉም። የማስረጃቸውን ምንጭ አንባቢ አረጋግጦ እንዲያምንላቸው አንድ እንኳን አላቀረቡም፣ አልጠቀሱም።

ሁለቱ ኃያላን በትጥቅ ትግሉ ጊዜ ነበራቸው ስለሚሉት ግጭቶችና አለመግባባቶች የጻፉት እውነት ሊሆን ይችላል በሚል መቀበል ጀምሬ ነበር። ዳሩ ግን በኋላ የሆነውን፣ እኛም  የምናውቀውን፣ ሲተርኩ ያሳዩት ሚዛናዊነት የጎደለው ማመሳሰልና ማነጻጸር የተለመደውን ካድሬያዊ የፕሮፓጋንዳ ሥራ በረቀቀ ዘዴ እየገፉበት መሆኑን እንድገነዘብ አድርጎኛል። ይፋ የሆነው የግጭታቸው መንስኤ አንዱን ለእስር ሌላውን ለፍጹም አምባገነንነት ያበቃው የኤርትራ ጉዳይ፣ የኤርትራ ጦርነት፣ በጦርነቱ ግብና ዓላማ ላይ የነበራቸው ልዩነት እንደነበር አገር የሚያውቀው ነው። 'አመድ ይዞ ከዱቄት' እንዲሉ ትንሽ እውነትን ከግዙፍ ውሸት ጋር ደባልቆ ታሪክ ልንገራችሁ ማለት የትዝብትና ቅሌት ማቅን ከመከናነብ በቀር ማራመድ የተፈለገውን ስውር ዓላማ ፈቀቅ የማድረግ ውጤት አይኖረውም።

በ'ቡርቃ ዝምታ' በአማራና በኦሮሞ ህዝብ መካከል ጸንቶ የቆየውን ተከባብሮ በሰላም አብሮ መኖር ጥቃቅን ቅራኔዎችን በማጉላት የጥላቻና የጥርጣሬ ዘር ዘርተዋል። በቦታውና በጊዜው አለመኖራቸው ግልጽ ሆኖ ሳለ በመጽሓፋቸው እከሌ እንዲህ አለ፣ እንትዬ እንዲህ ሲል መልስ ሰጠ ይሉናል-ከሳቸው ትውልድ በፊት ሆነ ስለሚሉት ነገር ጭምር።

በመሰረቱ የታሪክ ምሁርና ጸሐፊ ለመሆን መጀመሪያ የታሪክ ተማሪ መሆንን ይጠይቃል። የታሪክ ተማሪ ሳይሆኑ ወይም በምንጭነት የታሪክ መጽሐፍት ወይም ባለሙያ ሳይጠቅሱ ስለኢትዮጵያ ብሄር/ብሄረሰቦችና ጎሳዎች የጥንት ታሪክ ይተርኩልናል። ትረካው ደግሞ አፍራሽነት ያላቸውን አንዳንድ ቅራኔዎች የሚመለከት እንጅ ሌላውን ገጽታ ጭምር የሚዳስስ አይደለም። ቀደም ሲል የዘሩት የጥላቻና የመለያየት መጥፎ ዘር በኢትዮጵያዊነትና በአንድነት ሀይሎች ትግል እየተናደ ባለበት ባሁኑ ጊዜ ስልታዊ በሆነ ውብ ቃና ባለው ቋንቋ እንደገና የህዝቦችን አንድነትና መቀራረብ የሚፈታተን የጥላቻና ያለመተማመን ግርሻ ለመመለስ ጥረት እያደረጉ ነው።[7] የጎሳ ጥላቻን ለማራገብ እንዲያመቻቸው በኢትዮጵያ ማህበረሰብ ግንኙነት ላይ አዋቂው እኔ ብቻ ነኝ ለማለት ዳድቷቸዋል። ራሳቸውን የኦሮሞ ተቆርቋሪ ለማድረግ በመሞከራቸው፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በአንድ ወቅት "ተስፋዬ ከኦሮሞዎች በላይ ኦሮሞ ለመሆን ከመሞከሩም በላይ ከራሳቸው ከኦሮሞዎች የበለጠ ኦሮሞዎችን አውቃለሁ ባይ ነው" ማለታቸውን አስታውሳለሁ። ደራሲው የገለልተኛነትን ጥብቆ በማጥለቅ ለማሳሳት ቢሞክሩም፣ ገለልተኛ መሆን ከቶ አልተቻላቸውም። መጽሐፉ የገኘውን ፓርቲ አንዳንድ ባለስልጣኖች ማጋለጡ በዋናነት እንዲያመጣ የተፈለገ የሚመስለውን ጉዳት ስለማይመጥን በማር የተሸፈነ መርዝ አይደለም ብየ ለማመን እቸገራለሁ።

ደራሲ ተስፋዬ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሸፍቱ ከኤርትራውያን ተወልደው ያደጉ ናቸው። ሁለት አገር አላቸው-ተወልደው ያደጉበትና የዝርያ/የወላጆቻቸው ሀገር። ራሳቸው ለአዲስ ደምጽ ሬዲዮ  በሰጡት ቃለ ምልልስ ወላጆቻቸው ለኤርትራ ነፃነት ሪፈረንደም በመሳተፋቸው ደስተኞች እንደነበሩ ማወቃቸውን ገልጠዋል።[8] ኢትዮጵያ ቢኖሩም ኤርትራዊነትን መርጠዋል ማለት ነው። በተለያዩ ወቅቶች ስለኤርትራ ሪፈረንደምም ሆነ ኤርትራን ስለሚመለከቱ አንዳንድ ጉዳዮች አስተያየት ተጠይቀው ከማድበስበስ በስተቀር አንዴም ቀጥተኛና ትክክለኛ መልስ ሰጥተው አያውቁም። ሌላዋ አገራቸው ኤርትራም መቆየታቸውን ገልጠዋል። ለሁለት አገሮች እኩል ታማኝነት አስቸጋሪ ይመስለኛል። በአፋቸው ኢትዮጵያዊ፣ በድርጊትና በሚያራምዱት ስውር ዓላማ ግን ኢትዮጵያዊነትን ሳይሆን ኤርትራዊነትን ተቀብለው የሻቢያ አገልጋይ መስለው ነው

---

[6] ተስፋዬ ገብረአብ፣ <u>የደራሲው ማስታወሻ፣</u> ገጽ 292-293

[7] ተስፋዬ ገብረአብ፣ <u>የደራሲው ማስታወሻ፣</u> ገጽ 336-348

[8] http://www.ethiofact.com/index.php?/20090425451/content/tesfaye-gebreab.html ላይ እንደተጠቀሰው

የሚታዩት። እስካሁን ድረስ ስለሻቢያ በጎም ክፉም ሲናገሩ የሰማሁት የለም። የኢትዮጵያን ፖለቲካ ለማተራመስ የሰላ ብዕራቸውንና ቁጡ አንደበታቸውን ያለገደብ ሲያሰልፉ አንዴ እንኳን ኤርትራን ለመቃኘት እንዴት አልሆነላቸውም?

የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በዘመዶቻቸውና ወዳጆቻቸው ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያደረሰው ጉዳት እንዳለ አናውቅም። ግን ግልጽ ሆኖ የወጣ ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ሠራዊት የኤርትራን ምሽግ ሰብሮ ወደፊት መገስገሱ የኤርትራን ነፃነት ጉዳይ አደጋ ላይ በመጣሉ ኤርትራውያንን አሳስቦ የነበረ መሆኑ ነው። አቶ ተስፋዬም እንደወገኖቻቸው ሁሉ አላሳሰባቸውም፣ አልተጨነቁም ነበር ማለት ይከብዳል። እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ የፈጠረው በአቶ ስየ የሚመራው ቡድን ነው ብለውም ያምናሉ፣ እርግጥም ነው። ታዲያ አቶ ተስፋዬና በዚያ ጭንቀት ላይ የነበሩ ኤርትራውያን ወገኖቻቸው በአቶ ስየና አጋሮቻቸው ላይ ቁርሾ አልያዙም፣ አይዙም ማለት ይቻላል? በዚያን ወቅት ሁለት ኤርትራውያን ጓደኞቼ "ይህን የጭካኔ ሥራ መለስ አያደርገውም፣ የገብሩና የስየ ሥራ ነው" ብለውኝ እንደነበር አስታውሳለሁ። ከዚህ መንደርደሪያ በመነሳት አቶ ተስፋዬ ለኤርትራና ኤርትራ ላሉ ወዳጅ ዘመዶቻቸው ቢጨነቁና ቢያዳሉ፣ በአቶ ስየና አጋሮቻቸው ላይ ቂም ቢቋጥሩ የሰብዓዊ ተፈጥሮ ጉዳይ ስለሆነ ላይፈረድባቸው ይችላል። መጥፎ የሚሆነው ግን እንደበግ ለምድ ለባሿ ቀበሮ የኢትዮጵያዊነትን ካባ ለብሶና ተቀዋሚ መስሎ የሻቢያንና የመለስ/ወያኔን አጀንዳ አስፈጻሚ ሆኖ መገኘት ነው።

ተስፋዬ ስየን ከመለስ የከፋ ዘረኛ ነው ይላሉ። በትግላቸው ወቅትና ሥልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት ዘረኝነት አሳይተው እንደሆነ አላውቅም። ግን በተለይ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጊዜና በኋላ ኢትዮጵያዊ አጀንዳ አራማጅነታቸውን የሚክድ ችግር ያለበት ነው። ተስፋዬ የሚሉትን ተቀብለን ስየ ዘረኛ ነበሩ ብንል እንኳን የዘረኝነትን ግንብ ሰባብረው የወጡ ጀግና ናቸው ብለን እጃችንን ዘርግተን በደስታ እንቀበላቸዋልን። ስየ በተግባር እያረጋገጡ ያሉትን በመካድ እንደተስፋዬ አሁንም ዘረኛ ናቸው ብሎ ማላዘን የአንድነትና የኢትዮጵያዊነትን አጀንዳ መቦርቦር ይሆናል። መለስን ጨምሮ ሌሎችም ዘረኞች አይሆንላቸውም እንጅ ቢጀግኑና ቢቀላቀሉን ያገራችን አንዱ ዓቢይ ችግር በተፈታ ነበር፡፡

ስለስዬ ኢትዮጵያዊ  አጀንዳ አራማጅነት ግን ከተስፋዬ ይልቅ የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቃል። ዛሬ ኢትዮጵያዊ አጀንዳ አራማጅነቱን ያረጋገጠው መድረክ የተፈጠረው እንደስየና ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የመሳሰሉ የብሄር ፓርቲ መሪዎች የነበሩ ባደረጉት ጥረት ጭምር መሆኑ እንዴት ይካዳል? ስየ ህብረብሄር ፓርቲ በሆነው በአንድነት ውስጥ በከፍተኛ አመራር አባልነት ተቀባይነት ያገኙት ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም መቆማቸው በፓርቲው ዘንድ በመታወቁና የፓርቲውም አባላትና ደጋፊዎች ፍላጎት ስለሆነ ነው። አቶ ስየ ዛሬ በይፋ ለህዝብ ሲገልጹ የሚሰማው ስለኢትዮጵያዊነት አጀንዳ-ስለብሄራዊ እርቅ አስፈላጊነት፣ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ከጥላቻና ከመበቃቀል ወጥተው ሰላማዊ ዲሞክራሲያዊ ባህል ስለሚገነባበት ሁኔታ፣ ስለአገር አንድነትና ሉአላዊነት፣ በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የአሰብን ወደብ ኢትዮጵያ ስለምታገኝበት፣ ውሀን ጨምሮ ስለብሄራዊ ሀብታችን አጠቃቀም፣ ስለዲሞክራሲና የህግ ሉአላዊነት መከበር ጉዳይ ነው። እንዲህ የመሰለ በጎ ዓላማና ራዕይ ያለው ሰው በተቀዋሚ ፓርቲ አመራር ላይ መሆኑን እያወቁ፣ ራሳቸው ተስፋዬ እንደሚሉት እውነተኛ ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ካላቸው፣ ለምን አስነዋሪ የስም የማጥፋት ዘመቻ ያካሂዳሉ? መልሱ አንድም በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትና ከዚያም በኋላ በወሰዱት አቋማቸው 'ከኢትዮጵያዊ' የሚሰነዘር ትችት አስመስሎ የፖለቲካና ማህበራዊ ህይወታቸውን ጥላሸት በመቀባት መበቀል፤ አሊያም የአንድነት/መድረክ መጠናከር እጅግ ያሳሰበው መለስ/ወያኔ ተወዳጅ መሪውን አስሮ ስላልረካ ይልቁንም የስየ በአንድነት ውስጥ መግባት ይበልጥ ስላሸበረው በአመራሩ ላይ ጥርጣሬንና ፍርሃትን ለመፍጠር የወያኔን፣ ብሎም የሻቢያን ስውር ተንኮል ማራመድ ሊሆን ይችላል።

ከዚህም በላይ ተስፋዬ የጥቃት ስልታቸውን ለወጥ በማድረግ አደገኛው ስየ በመካከላችሁ ገብቶ የትግራይን የበላይነት የማስጠበቅ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ነው የኢትዮጵያዊነት አራማጅ መስሎ የመጣውና አማራ ሁሉ ተጠንቀቅ በማለት ፍርሃትንና ጥርጣሬን ለመፍጠር ሞክረዋል;፡ እባክዎን ተስፋዬ በእግዚአብሔር ይሆንብዎና ከከይሲና ከፋፋይ ተግባርዎ ይቆጠቡልን፤ ትግሬ፣ አማራ፣ ኦሮማ እያሉ መከፋፈልና ማስፈራራት ጊዜው ያለፈበት ካርድ እየሆነ ነውና አያበላም።

በአንድ ወቅት የአቶ መለስና ባለሟሎቻቸው ታላቅ ሥራ የነበረው አቶ ስየን በሙስና ወንጅሎ በሀሰት ክስና ምስክር ማሰር መሆኑ የሚታወቅ ነው። ለዚህም በቀረቡባቸው በርካታ የሀሰት ወንጀል ክሶች በዋስ ሆነው እንዳይከላከሉ የዋስትና መብት የሚነፍግ አዋጅ በአስቸኳይ በማውጣት ለስድስት ዓመት ካሰቃያቸው በኋላ የተፈቱበትን ሁኔታ አጥተውት ነው ብየ አልገምትም።

የመጽሐፋቸው አልበቃ ስላላቸው ይመስላል ከላይ በተጠቀሰው ፓልቶክ በአንድነት/መድረክ አመራር ላይ ዘመቻቸውን አጠናክረው ቀጥለዋል። እንደደራሲ በመጽሐፉ ላይ ያሰፈሩት በቂ በሆነ ነበር። ከዚያ አልፎ በየመድረኩ አጠንክሮ በሀሰት ስም ማጥፋትና መሳደብ ግን የተለየ ዓላማና ተልዕኮ ያላቸው መሆኑን አረጋጋጭ ነው። ተስፋዬ *"ብርቱካን ታሰራ እሱ (ስየ) ስልጣኗን ነጠቃት"* ብለዋል። *"እጅግ አደገኛ በሆነ ሁኔታ ነው ስየ ወደሥልጣን እየገሰገሰ ያለው"* [9] በማለትም የመለስ/ወያኔን ስጋትና ፍርሃት በመጋራት ገልጠዋል። የወ/ት ብርቱካን ወንበር እንዳለ መሆኑን፣ አቶ ስየ ተጠይቀውና ፈቅደው ወደፓርቲው ተቀላቀሉ እንጅ በአመጽ ስልጣን ለመቀማት እንዳልሄዱና እንዳልቀሙ እየታወቀ ልቅ የሆነ ውሸታቸውን ይፋ አድርገዋል። ተስፋዬ የሚፈልጉት አቶ ስየ በትግራይ የብሄር ፓርቲ ብቻ አባል እንዲሆኑ ነው? በዘር መደራጀት?

ቀጥለውም ወደአንድነት በአመራር ደረጃ የተቀላቀሉትን ዶ/ር ነጋሶን "የእግዚአብሔር በግ" ናቸው "እንደተቀዋሚም አልቆጥራቸውም" እያሉ ዘልፈዋል። ለመሆኑ ከፕሮፓጋንዲስት ካድሬነት ውጭ የተለየ እውቀትና ሙያ ሳይኖር፣ ወደኮሌጅ እንኳን ለመግባት በሚያስችል ትምህርት ላይ ሳይገኙ የላቀ ትምህርት (ፒኤችዲ)፣ ሰፊ ልምድና በፕሬዜዳንትነት ሀገርን የመራን ሰው እንዲህ አድርጎ መንቀፍ እብድነት አሊያም ጋጠወጥነት ነው።

ወደተቀዋሚው የተቀላቀሉትን የቀድሞ የኢህአዴግ አባላትንም በሙሉ *"ዲሞክራሲያዊነት ያመጣሉ፣ የህግ ሉአላዊነት አስከብረው ህዝቡ የሚመኘውን ዘመን ያመጣሉ ብየ አላምንም፣ ህልም ነው፣ የማይታሰብ ነው"* በማለት አማረዋል። አቶ መለስና ባለስልጣኖቻቸው በአንድነት/መድረክ ተቀዋሚዎቻቸው ላይ እያደረጉት ካለው የማጥላላት ዘመቻ በላቀ ሁኔታ የፕሮፓጋንዳ ሥራ እየሠሩላቸው ነው። ለምን ዲሞክራሲያዊነትን፣ የህግ የበላይነትን፣ ህዝቡ የሚመኘውን ዘመን እንደማያመጡ አይነግሩንም። በዲሞክራሲና በህግ ሉዓላዊነት መከበር ይበልጥ ተጠቃሚው አምባገነኑ ገዥ ፓርቲ ሳይሆን ተቀዋሚዎች እንደሆኑ ለማንም ግልጽ ነው- የህገወጥነትና የጸረ-ዲሞክራሲ ሰለባዎች ናቸውና። በዚህ የምርጫ ወቅት ጠብቆ በወጣው መጽሓፋቸውና መግለጫዎቻቸው ለገዥው ፓርቲ ያላቸውን አጋርነት በተግባር አረጋግጠዋል። በተለይ የአቶ መለስ ባላንጣ በመሆን ለፓርላማ አባልነት የሚወዳደሩትን ወ/ሮ አረጋሽንም ክፉኛ ተጠናውተዋል። ይህም ድጋፋቸው ለማን እንደሆነ ያሳያል። የአረና ፓርቲና የመድረክ ም/ሊቀመንበር የሆኑትን አቶ ገብሩ አስራትንም "ገብሩ ከስየ የከፋ ነው" በማለት ይገልጧቸዋል። ተስፋዬ ከታሪክ ጸሃፊነትና ከፓርቲ ፕሮፓጋንዲስትነት መካከል መምረጥ ግድ ይሆንባቸዋል። ስሜታዊነትንና ስድብኤልነትን ገና ስላላሸነፉ በልብወለድ ጸሃፊነት ቢገፉበት የደራሲነታቸውን ደረጃ እጅግ ባላቁት ነበር።

ተስፋየ ራሴን ነፃ አውጥቻለሁ የሚሉትን የቀድሞ የፖለቲካ ድርጅታቸውን በመደገፍ ተቀዋሚውን፣ በተለይም በአሰብ ጉዳይ ላይ ከመለስ የተለየ አቋም የወሰዱትን ቢታገሉ እየሠሩ ያሉት ሀገሬ ለሚሏት ለኢትዮጵያ ወይስ ለእናት አገራቸው ለኤርትራ? ልብ በሉ፣ በአሰብ ላይና የአልጀርሱን ስምምነትና የሄጉን ውሳኔ ውድቅ እናደርጋለን በሚሉት የአንድነት/መድረክ አመራር አባላት ላይ ሰፊ ዘመቻ እያካሄዱ ሲሆን፣ የአሰብን ጉዳይ አታንሱብኝ እያለ የአልጀርሱን ስምምነት ፈርሞ ላጸደቀውንና የሄጉንም ፍ/ቤት ውሳኔ ለተቀበለው ለአቶ መለስ ቡድን የፕሮፓጋንዳ ድጋፍ በመስጠት ላይ ናቸው። ታዲያ አቶ ተስፋዬ ማን ናቸው? የኢትዮጵያ ወይስ የኤርትራ ጥቅም አስከባሪ ፕሮፓጋንዲስት?

በመጨረሻ ሳላወሳው የማላልፈው አንድ ጉዳይ አለ። በመልካም አጻጻፍ ተለውሶ እንዲህ የመሰለ መሰሪነትን ያካተተ መጽሐፍ የማከብራቸውንና ደጋፊያቸው የሆንኩትን የዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ቡራኬ ማግኘቱ አስገርሞኛል፣ አሳዝኖኛል። ዛሬ ዶ/ር ብርሃኑ የሚመሩት ድርጅትና የደራሲ ተስፋዬ ብዕር ካነጣጠረባቸው እነአቶ ስየ በአመራር ከሚገኙበት ከአንድነትና መድረክ የትግል ስልት ልዩነት ቢኖራቸውም የግብ ልዩነት አላቸው ብየ አላምንም። ለተመሳሳይ ግብ መዳረሻ እንቅፋቶችን በጋራ መታገል አስፈላጊ ነው ባይ ነኝ-የርስ በርስ መጠላለፍ ይብልጥ የሚጠቅመው ገዥውን ፓርቲ ነውና። የተስፋዬ ብዕር የመለስን አምባገነናዊ አገዛዝ ባለስልጣናት ያጋለጠ መስሎና ወቅት ጠብቆ በአንድነት ፓርቲ አመራር ላይ ጥርጣሬ በሚፈጥር ሁኔታ ያቀለመውን ጽሁፍ ዶ/ር ብርሃኑ ደግፈዋል። ወያኔን ስላጋለጠ ተብሎ አጋሮችን የሚጎዳ፣ ከህቅ ይልቅ በስሜታዊነት ላይ የተመሰረተን ጽሁፍ ተስማምተው ሲደግፉ የራሳቸውም ሀሳብ ጭምር አድርገው ተቀብለውታል ብየ እገምታለሁ። ዶ/ር ብርሃኑ ይህን ያደረጉት ጠንካራ አጋር ተቀዋሚ የፖለቲካ ድርጅት መኖርን ካለመሻት ነው ብየ ለማመን ግን ይቸግረኛል። ጽሁፉን ያለአንዳች ቅናሽ እንዳለ በመደገፍ የደራሲውን አቋም ሁሉ የራሳቸው ማድረጋቸው ስህተት ስለሆነ በይፋ ይቅርታ ሊጠይቁበት ይገባል ባይ ነኝ።

---

[9] http://ecadforum.com/blog/?p=3643